**ለሚቀጥለው የትምህርት አመት አስቀድመህ አቅድ**

Montgomery County የትምህርት ቦርድ የ2014-2015 የትምህርት አመትን ቀን መቁጠሪያ አጽድቋል።

ትምህርት የሚጀምረው ሰኞ፣ ኦገስት 25 እና የሚጨረስበት ጊዜ ደግም አርብ፣ ጁን 12 ነው። የስፕሪንግ ዕረፍት ከኤፕሪል 6-10 ባለው ሳምንት ይሆናል።

የቀን መቁጠሪያውን ከMCPS ድረ ገጽ ማተም ይቻላል። በቅርቡ በሰባት ቋንቋዎች ይገኛል-አማርኛ፣ ቻይንኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ኮርያኛ፣ ስፓኒሽኛ እና ቬትናምኛ።

የቀን መቁጠሪያው የተዘጋጀው በMontogomery county Council of PTAs፣ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ሶስት የሰራተኛ ማህበራት፣ እና Montogomery County of the Maryland Association of Student Councils እንዲሁም ሌሎች የማህበረሰብ አባላትና የትምህርት ስርአት አመራር ጋር በሽርክና በመስራት ነው።

[ለሚመጣው የትምህርት አመት ጠቃሚ የሆኑ ሁሉን ቀናት ይመልከቱ]።

**የትምህርት ቤቶች የበላይ ሃላፊ የMCPS 2ኛውን አመታዊ የትምህርት ቤቶች ጉባኤ ያደርጋል።**

የትምህርት ቤቶችን የበላይ ሃላፊ ጆሹአ ስታር ኖቬምበር 10 በስትራዝሞር የሙዚቃ ማዕከል ባደረገው የሁለተኛ አመታዊ የትምህርት ቤቶች ጉባኤ ንግግር ከ750 ሰዎች በላይ ተገኙ። ድርጊቱ የMCPS ማህበረሰብ የMCPS ተማሪዎችን ስኬትና ስጦታ ለማክበር በጋራ እንዲሆኑ እንዲሁም ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ስኬት ዲስትሪክቱ ሁሉን ተማሪዎች እንዴት እያዘጋጀ እንደሆነ የዶ/ር ስታርን ራዕይ ለመስማት አስችሏል።

ከንግግሩ መቅረብ በፊት እንግዶች በMCPS ተማሪዎች በተዘጋጁ ድንቅ ሙዚቃና ውዝዋዜ ተጋብዘዋል፣ እናም የተማሪዎችን ኪነ-ጥበባዊ ስራ ለማየት ዕድል አግኝተዋል። በድርጊቱ ከ39 MCPS ት/ቤቶች ከ100 በላይ ተማሪዎች ተሳትፈዋል።

የ2013 የት/ቤቶች ጉባኤ ድርጊት ለመካሄድ የቻለው በ ስትራዝሞር እና ግሊንስቶን ድጋፍ ነው። የእነርሱ ድጋፍ ከእነዚህ ድርጅቶች ጋር MCPS የነበረውን ሽርክና የሚያጠንክር ነው። የሙዚቃ ማዕከሉ ከተከፈተ 2005 ጀምሮ Strathmore Student Concert Series ኮንሰርቶችን ያቀረበ ሲሆን National Philhamornicም ለሺዎቹ የMCPS ተማሪዎች በየአመቱ አቅርል። ግሊንስቶን ከዲስትርክቱ ጋር ሽርክና

የጀመረው በ2011 ሲሆን በመቶዎች የሚቆጠሩ መምህራንና ተማሪዎች ሙዚየሙን እንዲጎበኙ እና በአገሪቱ በጣም የታወቁ ዘመናዊ ኪነ-ጥበብ ስብስቦችን ለማየት አስችሏል።

የ2013 የት/ቤቶች ጉባኤ ሊዘጋጅ የቻለው በሌሎች ሽርኮችም ጭምር ሲሆን ይህም Pepco፣ International Baccalaurete፣ Comcast፣ Hess Construction and Engineering፣ እና Montgomery County Business Roundtable for Education ያካትታል።

ከድርጊቱ የተገኙ ገቢዎች ሁሉ የMontgomery County Public Schools Educational Foundation ተልዕኮ ለመደገፍ የሚያገለግሉ ሲሆን በተለይም Achieving Collegate Excellence and Success (ACES) ፕሮግራምን ነው። ACES ፕሮግራም በMCPS፣ Montgomery College፣ እና Universities at Shady Grove የጋራ ጥረት ሲሆን ይህም በከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ዕድል ላላገኙ ተማሪዎች ኮሌጅ መግባትና ማጠናቀቅን ለማሻሻል ነው። የበለጠ ለማወቅACES ድረ ገጽ።

ድርጊቱን የሚመለከት ቪዲዮና ፎቶዎችበት/ቤቶች ጉባኤ ድረ ገጽ ወጥተዋል።

**የትምህርት ቦርድ $1.74 ቢሊዮን የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም ያጸድቃል**

Montgomery County የትምህርት ቦርድ $1.74 ቢልዮን ለስድስት አመት የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም (CIP) አጸደቀ ይህም በMCPS የተጠየቀ ሲሆን በየእመቱ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ባለው የምዝገባ እድገት ምክንያት የተፈጠረውን መጨናነቅ ለማቃለል የሚያግዝ ይሆናል። ጥያቄው የሚያካትተው 14 አዲስ መማሪያ ክፍሎች ተጨማሪ ፕሮጀክቶች እና የትምህርት ቤቶችን አቅም የሚጨምሩ አያሌ ሌሎች ፕሮጀክቶችን በታቀደው እንዲቀጥሉ ነው። ለ2015 የበጀት እመት (FY) የካፒታል በጀት የተጠየቀው $251.6 ሚልዮን ነው።

በየሁለት አመት አዲስ የስድስት አመት CIP ይፀድቃል እናም በአራት አጠቃላይ ክፍሎች የመዋእለነዋይ ፈሰስ ያካትታል — እንደ አዲስ ት/ቤቶችን ተጨማሪ መማርያ ክፍሎች የመሳሰሉ የስፋት አቅም ፕሮጀክቶች፤ነፍስ-ዘሪ/የመስፋፋት ፕሮጀክቶች ያሉትን ትም/ቤቶች የሚያድሱና የሚያስፋፉ፤ ታህታይ መዋቅር ማሻሻያዎች፤ እና ቴክኖሎጂ።

የቦርዱ CIP ጥየቃ ከአሁኑ CIP (FY 2013-2018) በ$376.5 ሚልዮን የሚበልጥ ሲሆን ነገር ግን ከዲስትሪክቱ ተጨባጭ ፍላጎት በጣም ያነሰ ነው። ሁሉንም የዲስትሪክቱን አንገብጋቢ የግብአቶች፣ መሰረተ ልማትና ቴክኖሎጂ ፍላጎቶች ለማሟላት የ$2.2 ቢልዮን CIP ያስፈልጋል።

የቦርዱ CIP ጥየቃ ለCounty Executive እና County Council እንዲመለከቱት በቅርቡ የሚቀርብ ይሆናል። የCounty Executive የራሱን CIP የሚመለከት ለካውንቲው የMCPSን ጨምሮ በጃንዋሪ ያቀርባል። ቦርዱ የCIP ጥየቃን በስፕሪንግ ይመለከታል።

የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ጆሹአ ፒ. ስታር $1.55 ቢልዮን የCIP አስተያየቱን ኦክቶበር 28 አስረክቧል። ቦርዱ የጠየቀው CIP ከዶ/ር ስታር አስተያየት በ$192.6 ሚልዮን አካባቢ የሚበልጥ ሲሆን ምክንያቱም በማህበረሰብ ተሳትፎና በዲስትሪክት አቀፍ ፍላጎት በመመስረት ቦርዱ ባደረገው ለውጥ ነው።

በCIP ላይ የህዝብ አስተያየት ኖቬምበር 11 እና 14 ተካሂዶ የነበረ ሲሆን በመቶዎቹ የሚቆጠሩ ተማሪዎች፣ ሰራተኞች፣ ወላጆች እና የማህበረሰብ አባላት ተገኝተዋል። ብዙ ትኩረት የነበረው በቦታ እጥረት ላይ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን በማርጀት ላይ ያሉ ህንጻዎችና መሰረተ ልማቶችን ማደስን በተመለከተ እያደገ ያለውን ፍላጎትም ጭምር ነበር።
[ተጨማሪ ይማሩ]

**Walk Your Way! (በአራስዎ መንገድ ይጓዙ!)**

Montgomery County Department of Transportation የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ስለ እግረኛ ደህነነት አስፈላጊነት ማስተማርን ለማገዝ Walk Your Way የሚል ፕሮጀክት ሊጀምር ነው። ካውንቲው የእግረኛ ደህንነትን በየሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤታቸው ለማስተማር ያሚያስችል ፕሮግራም ለሚፈጥሩ፣ ለሚነድፉና ለሚተገብሩ የሀለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ቡድኖች የሚሆን እስከ $2 000 ይሸልማል። ፕሮጀክቶች የእግረኛ መጓዣን ከመቀባት ጀምሮ፣ በራሪ ጽሁፎችና ሌሎች ቁሳቁሶችን መንደፍና ማሰራጨት፣ የትምህርት ቤት ጎባኤ ማድረግ ድረስ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ስጦታ ብቃት ለማግኘት ተማሪዎች ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በመሆን በቡድን መስራት ግዴታ ሲሆን በድጋፍ ሰጪነትም ቢያንስ አንድ መምህር ወይም ሰራተኛ ተቆጣጣሪ መኖር ያስፈልጋል። ፕሮጀክቱን ከኤፕሪል 30 2014 በፊት ማዳበርና መተግበር ግዴታ ነው። የማመለልከቻዎች የጊዜ ገደብ ሰኞ ዲሴምበር 16 በ5 p.m ነው። በሚከተለው ኢ-ሚይል ማስገባት/ማስረከብ walkyourway@montgomerycountymd.gov ወይም 101 Monroe Street 10ኛ ፎቅ Rockville በእጅ መስጠት ይቻላል።

ለተጨማሪ መረጃ Nadji Kirby ወይም Alex cohen ይገናኙ n walkyourway@montgometycountymd.govወይም click hereይህን ይጫኑ።

**MLK እና Gaithersburg Book Festival Literary ውድድሮች ለMCPS ተማሪዎች ክፍት ናቸው።**

የMCPS ተማሪዎች በሚከተሉት የጽሁፍ ውድድሮች ለመሳተፍ እድል አላቸው፡

*2014 MLK Literary Contest & Visual Arts Show*

በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ያሉ ተማሪዎች በDr. Martin Luther King, Jr Literary Contest & Visual Arts Show እንዲሳተፉ ይበረታታሉ። የ2014 ጭብጥ "Honoring the Legacy: Celebrate, Serve, Remember" ነው። መጣጥፎች እና የኪነ-ጥበብ ስራዎች የዶ/ር ኪንግን ህይወት፣ ስኬት እና ፍላጎት መረዳትንና ማድነቅን የሚያንጸባርቁ መሆን አለባቸው።
[ተጨማሪ መረጃ].

**የማስረከቢያ ጊዜ ገደብ 5 p.m አርብ ዲሴምበር 6 ነው።**

ውድድሩን ስፖንሰር ያደረጉት፣ Dr. Martin Luther King, Jr Commemorative Committee፣ Gaithersburg ከተማ*Gazette*ጋዜጣ ናቸው።

*Gaithersburg Book Festival (የመጽሀፍ ትርኢት)*

Gaithersburg Book Festival (የመጽሀፍ ትርኢት) በዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን አካባቢ ለሚኖሩ ከ9-12ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የአጭር ልብወለድ ውድድር ያካሂዳል። አጭር ልብወለዶች ከ1,000 ቃላት ያልበለጡ እና በመወዳደሪያ ድረ ገጽ ከተጠቀሱት ከሶስት መስመሮች ውስጥ በአንዱ መጀመር ግዴታ ነው። **ውድድሮችን በኤሌክትሮኒክ መልክ በMicrosoft Word ሰነድ ከፌብሩዋሪ 21፣ 2014 በፊት ማስረከብ ያስፈልጋል።** አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ደረጃ አሸናፊዎች በመጽሀፍ ትርኢቱ (Book Festival) ወቅት ቅዳሜ ሜይ 17፣ 2014 ይገለጻሉ።

ለተጨማሪ መረጃ የጋይተርስበርግ መጽሀፍ ትርኢትን ድረ ገጽይጎብኙ።

**እንዳይረሱ...**

በአንደኛው ሴምስተር የተካሄዱ ሁሉ አገልግሎት ሰነድ ለትምህርት ቤቱ SSL አስተባባሪ አርብ ጃንዋሪ 3 ከመድረሱ በፊት ማስረከብ ግዴታ ነው። ሁሉም ተማሪዎች እንዲጠቀሙ የሚገባቸው ቅጽ MCPS Form 560-51: Student Service Learning Activity Verification ነው። ስለ Student Service Learning (የተማሪ አገልግሎት መማር) ፕሮግራም እና የምረቃ መስፈርት የSSLድረ ገጽይጎብኙ።

**እንዲሁም...**

*ጎርቤት ለጎረቤት*

የጎረቤት ለጎረቤት (N2N) ዘመቻ በመካሄድ ላይ ነው። በMCPS የስራ ማስኬጃ በጀትና የደወል ሰአቶች ላይ በN2N ውይይት ወቅት ለመሳተፍ እድል አልዎት። ለተጨማሪ መረጃ የጎረቤት ለጎረቤት ድረ ገጽ ይጎብኙ።

***በደወል ሰአቶች ላይ የማህበረሰብ መድረኮች***

በሚቀጥሉት ወራት Montgomery County Public Schools (MCPS) የደውል ሰአቶች ተብለውም በሚጠሩት የትምህርት መጀመርያና መጨረሻ ሰአቶች የቀርቡ ለውጦችን በሚመለከት አስተያየቶች ለመስጠት በርካታ እድሎችን ይሰጣል። ይህም የማህበረሰብ መድረኮች፣ የትኩረት ቡድኖችና ዳሰሳዎች/መጠይቆች፣ እና በራስ የሚመራ ጉድዩን ለማጥናትና አስተያየት መስጫ የሆነውን "ጎረቤት ከጎረቤት"ን ያካትታል።

በመድረኮች ላይ ጥያቄዎችን የመጠየቅ ዕድል ይኖርወታል እናም በትምህርት ቤቶች የበላይ ሃላፊ ጆሹዋ ስታር አስተያየት በሆነው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ50 ደቂቃ ዘግይተው እንዲጀምሩ፣ መካከለኛ ትምህርት ቤቶች 10 ደቂቃ ቀደም እንዲሉ፣ እና የኤሌሜንታሪ ትምህርት ቀን በ30 ደቂቃ እንዲራዘም ምላሽዎን ያጋራሉ። የመጀመሪያው ማህበረሰብ መድረክ ኦክቶበር 28 ተካሂዷል። የሌሎቹ ሶስት ማህበራዊ መድረኮች እለቶችና ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው፡

**-ሰኞ ዲሰምበር 16፡** Richard Montgomery High School, 250 Richard Montgomery Drive in Rockville

**-ሰኞ ጃኑዋሪ 6፡** Seneca Valley High School, 19401 Crystal Rock Drive in Germantown

**-ሰኞ ፌብሩዋሪ 10፡** Montgomery Blair High School, 51 University Blvd, East, in Silver Spring

ሁሉም መድረኮች የሚከናወኑት ከ7 p.m. –8:30 p.m. ነው። ነፃ የልጆች (4 አመትና ከዚያ በላይ) እንክብካቤና የትርጉም አገልግሎቶች ይኖራሉ።

ተጨማሪ መረጃ

**Montgomery County Recreation Guide በአሁኑ ወቅት ይገኛል።**

የዊነተር ወራት ህትመት Montgomery County Guide for Recreation and Parks Programs በአሁኑ ወቅት ይገኛል። ብዙ ፕሮግራሞች ቶሎ ስለሚሞሉ የMontgomery County ነዋሪዎች ቶሎ እንዲመዘገቡ እናደፋፍራለን። መመሪያው በመቶዎች የሚቆጠሩ ፕሮግራሞችና እንቅስቃሴዎች ያቀፈ ሲሆን የውሃ ተግባራት/እንቅስቃሴ፣ ኪነ ጥበብና የእጅ ስራ፣ ስፖርትና ውዝዋዜ (ዳንስ) ያካትታል።

መመርያውን በኮምፒውተር ለማየት Department of Recreation ድረገፅይጎብኙ። የታተሙ ቅጂዎች በመዝናኛ ማእከሎች፣ በመናፈሻ መገልገያዎች፣በመንግስታዊ ህንፃዎችና ቤተመፃህፍት ይገኛሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ 240-777-6840 ይደውሉ።